# የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት

## ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ መራጭ የተሳተፈበትና ሰላማዊና በስርዓት የተካሄደ ሆኖ በጠባብ የፖለቲካ ክልልና ባልተደላደለ የመጫወቻ ሜዳ የታጠረ ሂደት፡፡

### አዲስ አበባ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ ጋባዥነት እንዲሁም በሁለቱ ወገኖች መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን (ልዑክ) ግንቦት 15/2002 ዓ.ም ለተወካዮች ምክር ቤትና ለክልል ምክር ቤቶች የሚካሄደውን ብሔራዊ ምርጫ ለመታዘብ ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል፡፡ የአውሮፓ የፓርላማ አባል በሆኑት በታይስ በርማን የሚመራው ልዑክ ዋና የተንታኝ ቡድንን አካቶ ሚያዝያ 6 አዲስ አበባ የደረሰ ሲሆን 90 የሚሆኑ የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች ሚያዝያ 16/2002 ዓ.ም ልዑኩን ተቀላቅለው በመላው አገሪቱ ተሰማርተዋል፡፡ የምርጫ ታዛቢው ልዑክ የህግ ማዕቀፎችን የምርጫ ባለስልጣናትን ስራ፣ የፖለቲካ ሁኔታውን፣ የምረጡኝ ዘመቻን፣ ለምርጫ የሚደረጉ ዝግጅቶችን ምርጫውን ተከትሎ የሚመጡ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን ድምፅ አሰጣጡን ጨምሮ የድምፅ ቆጠራውን አጠቃላይ የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ የተሰማራ ልዑክ ነው፡፡ ልዑኩ የምርጫውን ሂደት በኢትዮጵያ ህገ-መንግስትና ሌሎች ህጐች፣ እንዲሁም በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ደረጃ የተደረሱ ዴሞክራሲያዊ መለኪያዎች መሠረት መካሄዱን ገምግሟል፡፡

ልዑኩ ከማንኛውም አካል ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት በተዘጋጀው የዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢ አዋጅ መርሆችና የስነ-ምግባር ደንብ መሠረት ምርጫውን ታዝቧል፡፡ በምርጫው ዕለት ቡድኑ ከ23 አባል ሀገራት እንዲሁም ከካናዳ፣ ኖርዌይ እና ስዊዘርላንድ በተውጣጡ 170 ታዛቢዎች በ815 የምርጫ ጣቢያዎች በመላ ሀገሪቱ የድምፅ አሰጣጡን እና ቆጠራን ተመልክቷል፡፡ ልዑኩ የምርጫው ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከምርጫ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራትን እየተከታተለ የመጨረሻው ውጤት እስከሚገለጽ በሀገሪቷ ውስጥ ይቆያል፡፡ ይህ ሪፖርት

የመጀመሪያ ደረጃ ነው፡፡ ልዑኩ የምርጫው ሂደት እስኪጠናቀቅ የመጨረሻው ውጤት እስኪገለጽ የመጨረሻ የሆነውን ሪፖርት እያቀረቡም የመጨረሻው ሪፖርት የምርጫው ሂደት ከተጠናቀቀ ከሁለት ወር በኋላ ይፋ ይሆናል፡፡

**የአፈፃፀም ማጠቃለያ**

- ለአራተኛ ዙር ለተወካዮች ምክር ቤትና ለክልል ምክር ቤቶች መቀመጫ የተካሄደው ምርጫ ሰላማዊ በሆነ መልኩ በሚመለከታቸው አካላት ሙሉ ተቀባይነት ተፈጽሟል /ተካሂዷል/፡፡ በአንፃሩ ረጋ ብሎ በተቃዋሚዎችና በገዢው በኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ ሲካሄዱ የነበሩት የምረጡኝ ዘመቻ ወደ ማብቂያው አካባቢ

ሞቅ ብለው ተገኝተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድም ኃላፊነቱን በብቃትና በንቃት የተወጣ ቢሆንም በገለልተኝነቱ ግን የተቃዋሚዎችን ዕምነት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ በርካታ በጐ ጐኖች ቢኖሩትም የምርጫው ሂደት አንዳንድ አለምአቀፍ ደረጃዎችን ለመጠበቅ የተሳነው ነበር፡፡ ግልፅነት እና ለተቃዋሚዎች ምቹ የመጫወቻ ሜዳ አለመኖሩ በዚህ ረገድ እንደጉድለት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- ምርጫው በከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ በሰላማዊ መንገድ ተካሂዷል፡፡ ምንም እንኳ አንዳንድ እንከኖች ቢኖሩትና ወጥ የሆነ የአሰራር ሂደት በሁሉም ቦታ ባይስተዋልም የምርጫው ሚስጥራዊነት የጠበቀ ሆኖ ምርጫው ተካሂዷል፡፡ ቡድኑ በደረሰበት በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች የፓርቲ ተወካዮችና የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ተገኝተው ነበር፡፡
- በአጠቃላይ በሀገሪቷ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ አንፃራዊ ፀጥታ የነበረው ቢሆንም የምርጫው ቀን እየቀረበ በመጣበት ጊዜ በበርካታ የምርጫ ክልሎች አካባቢያዊ ውጥረት ነግሶ ነበር፡፡ በተመሳሳይ የምረጡኝ ዘመቻውም በሰላማዊ መንገድ የተከናወነ ሲሆን እስከመጨረሻው የምረጡኝ ዘመቻ ቀን የነበረው እንቅስቃሴ ግን እስከዚህም ነበር፡፡
- በበርካታ የክልል አካባቢዎች ባሉ የምርጫ ክልሎች በገዢው ፓርቲ እና በሕዝብ አስተዳደራዊ ሂደት ልዩነት አይታይም ነበር፡፡ የህዝብ ሀብት ለገዢው ፓርቲ የምርጫ ዘመቻ እንደዋለ በአንዳንድ በታ ልዑኩ በቀጥታ ተመልክቷል፡፡ ልዑኩ የ2002 ምርጫ ሚዛናዊነት የጐደለው ለገዢው ፓርቲ ያጋደለ መሆኑን በብዙ ቦታዎች ተመልክቷል፡፡ የመጫወቻ ሜዳው ሚዛናዊ አልነበረም፡፡
- ከ1997 ምርጫ በኋላ የአውራ ፓርቲዎች ሃይል መዳከም፣ አሉ የሚባሉ ተቃዋሚዎች ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ መገለላቸው ከህግ ማዕቀፍ ለውጡ ጋር ተዳምሮ በአጠቃላይ የፖለቲካው ሜዳ በሀገሪቷ ውስጥ እንዲጠብ አድርጓል፡፡
- የኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍ አህጉራዊና አለምአቀፍ ስምምነቶች በጠበቀ መልኩ በሀገሪቱ ምርጫ እንዲካሄድ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በተግባር ሲታይ የምርጫው ሂደት በአንዳንድ ገጽታው ከስምምነቶቹ ያፈነገጡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የምርጫ ሂደቱ ላይና ያለልዩነት መብትን የመጠቀም ዕድል ላይ ማነቆ ሆኗል፡፡
- በአጠቃላይ ምርጫ ቦርድ ዋና ዋና ቴክኒካዊ ፈተናዎችን በመላው የምርጫው ሂደት በብቃትና በስኬት አከናውኗል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ውጥረቶች በተለይ በምርጫ አስፈፃሚዎች ዘንድ የሂደት ወጥነትና የቴክኒካዊ መረጃዎች አጠቃቀም ለምሳሌ የምርጫ ጣቢያዎች ዝርዝርን አሟልቶ በማሳየት ረገድ ያለው የሂደቱን ግልፅነት ላይ እንከን የፈጠረ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ የምርጫ ቦርዱን ገለልተኝነት በተቃዋሚዎች አይን ተአማኒ ለማድረግ የተወሰደው እርምጃም አነስተኛ ነበር፡፡ በተለይ በምርጫ ክልል ደረጃ በብሔራዊ ደረጃና በአብዛኛው የምርጫ ክልሎች የሚገኙት የምርጫ አስፈፃሚዎች በእጅጉ ሲረዱ ነበር፡፡
- ከ37 ሚሊዮን ዕድሜው ለመምረጥ ከደረሰው ሕዝብ 32 ሚሊዮን ያህሉ ለ2002 ምርጫ በመመዝገብ ድምፁን ሰጥቷል፡፡

- ባለፉት አምስት ዓመታት ከምርጫ ቆጠራና ድምፅ አሰጣጥ እንዲሁም ውጤት ጋር በተያያዘ የሚመጡ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ የሚደረገው ጥረት የተጠናከረ ነበር፡፡ ይሁን እና ልዑኩ ከዚህ በተጨማሪ ከምርጫ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ቅሬታዎችን በህጋዊ መንገድ ለመፍታት ሌሎች ስራዎችም መሠራት እንዳለባቸው ተገንዝቧል፡፡ በተለይ የሕግ ተርጓሚውና ሕግ አስፈፃሚው አካላት ነፃና ገለልተኛ እንዳልሆኑ እምነት በሌላቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጉዳይ ለማየት፡፡
- በርካታ የሆኑ ቅሬታዎች የምረጡኝ ዘመቻውን በተመለከተ የተነሱ ችግሮች ላይ ማስፈራሪያዎችና በደሎች እንዲሁም ብጥብጥ እንደነበረ ከገዢው ፓርቲም ከተቃዋሚዎችም ተሰምቷል፡፡ በአጠቃላይ የምርጫው ሂደት ሲታይ እነዚህ ጉዳዮችም መታየት አለባቸው ልዑኩ የሁሉም ፓርቲ ታዛቢዎች ከማስፈራሪያና ዛቻ ነፃ ሆነው ዘመቻውን ማካሄድ እንደነበረባቸው ያምናል፡፡
- በአጠቃላይ መገናኛ ብዙሃኖችም ገለልተኛ በመሆን ዋና ዋና የፖለቲካ ፓርቲዎች ያካሄዱትን የምረጡኝ ዘመቻ ዘግበዋል፡፡ የመንግስት ሚዲያዎች በዜና እወጃዎች ወቅት ከ50% በላይ የሆነውን ጊዜ ለገዢው ፓርቲ አውለውታል፡፡ ነፃ የአየር ሰትም ለተለያዩ ፓርቲዎች የተከፋፈለበትም ሁኔታ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ሚዲያዎች በዘገባዎቻቸው ጠንቃቃ ነበሩ፡፡ የVOA የአማርኛ ፕሮግራም በመታፈኑ መራጮች በስተመጨረሻ አካባቢ የተደረጉ ዘመቻዎች ላይ የነበሩትን ስፋት ያላቸው መረጃዎች እንዳያገኙ ከልክሏቸዋል፡፡
- ምንም እንኳ የሴቶች ተሳትፎ በምርጫ ጣቢያዎች ከሌሎች የምርጫ ቦርድ እንቅስቃሴ አካባቢ ከፍ ያለ ቢሆንም በአጠቃላይ በምርጫ አስፈፃሚነቱ ዙሪያ ቁጥራቸው አነስተኛ ነበር፡፡ በአብዛኛው የፖለቲካ ፓርቲዎች እጅግ ጥቂት ሴቶች ናቸው የተወከሉት፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ ብቻ በ30% ኮታው መሠረት ሴቶችን በዕጩነት አቅርቧል፡፡ ከምርጫ 1997 ጋር ሲነፃፀር በአሁኑ ምርጫ የሴቶች ዕጩዎች ቁጥር ቀንሷል፡፡

## *የመጀመሪያ ደረጃ ግኝቶች*

ደርግ ከተገረሰሰ ከ1983 ዓ.ም በኋላ ኢትዮጵያ አራተኛውን ዙር ብሔራዊ ምርጫ በግንቦት 15/2002 ዓ.ም አካሂዳለች፡፡ የተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫዎች በአንድ ጊዜ ተካሂዷል፡፡ በሁሉም በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆንና የ1997ቱ ብጥብጥ እንዳይደገም ስምምነት ተደርሷል፡፡

የሀገሪቷ የፖለቲካ ገጽታ ከቀድሞው ምርጫ በኋላ የተለወጠበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ የፓርቲዎች መሰነጣጠቅ፣ መዋሃድና አዳዲስ ፓርቲዎች መፈጠር እንዲሁም አሉ የሚባሉ የፖለቲካ ሰዎች ከሀገሪቷ ፖለቲካ ተገለዋል፡፡ በምርጫ ቦርድ ከተመዘገቡት 79 ፓርቲዎች 63ቱ ዕጩዎቻቸውን ለ2002 ምርጫ አቅርበዋል፡፡ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ 501 ዕጩዎችን አቅርቧል፡፡ ለተወካዮች ምክር ቤት መድረክ ከተቃዋሚዎች ከፍተኛውን ቁጥር ያቀረበ ሲሆን ይኸውም 421 ዕጩዎች ናቸው፡፡ የመላው ኢትዮጵያ

አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ እሱን ተከትሎ 319 ዕጩዎች ሲያቀርብ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /ኢዴፓ/ 230 ዕጩዎችን ለወካዮች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡

**የህግና የምርጫ ሁኔታ**

ምርጫውን ፍፁም በሆነ ሰላማዊ መንገድ ለማካሄድ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት፣ በፀደቀው የስነ-ምግባር ደንብ እንዲሁም ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ በወጡ የምርጫ ህጐች መሠረት ተካሂዷል፡፡ የምርጫ ቦርድም የምርጫውን ሂደት በሚመለከት በርካታ መመሪያዎችንና ደንቦችን አዘጋጅቶ ነበር፡፡

ለወካዮች ምክር ቤት ለሚደረገው ውድድር በሀገሪቱ ውስጥ 547 መቀመጫዎች ለውድድር ቀርበዋል፡፡ ከምርጫ ክልሎቹ የሚያሸንፍ አንድ ነጠላ ተወዳዳሪ መቀጫውን ይይዛል፡፡ በየክልሉ ያሉትም የምክር ቤት መቀመጫዎች በተመሳሳይ መልኩ እንደየክልሉ ህግ ለውድድር ቀርበዋል፡፡

በህገ-መንግስቱና በምርጫ ህግ መሠረት ለአብላጫ ብሔሮች 22 መቀመጫዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ምንም እንኳ አናሳ ብሔሮችን የፓርላማ ተወካዮች ማድረግ ቢያስመሰግንም በእነዚህ የምርጫ ክልሎች አካባቢ ያለው የሕግና የአሰራር ሂደት ግልፅነት ይጐድለዋል፡፡

የምርጫ ክልሎችን ወሰንም ከ15 ዓመት በት በተዘጋጀው መሠረት ነው የተቀመጡት፡፡ ከምርጫ ቦርድ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው በአማካይ በብሔራዊ ደረጃ በአንድ የምርጫ ክልል 53,500 /ሃምሳ ሶስት ሺህ አምስት መቶ/ መራጮች ይኖራሉ፡፡ በክልሎች መካከልም ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡ በቤንሻንጉል ጉምዝ ከ40,000 /አርባ ሺህ/ በላይ መራጮች ሲኖሩ በአፋር ደግሞ ቁጥሩ ወደ 130,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ/ ይጠጋል፡፡ ይህ ደግሞ ከድምፅ እኩልነት መርህ ጋር ይጣረሳል፡፡

አህጉራዊና አለምአቀፋዊ የስምምነት ህጐች መሠረትን ባደረገ በኢትዮጵያ ትክክለኛ ምርጫ ለማድረግ የኢትዮጵያ ህግ ይደነግጋል፡፡ ይሁንና የህጉ አፈፃፀም ባንዳንድ መልኩ እነዚህን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በምርጫው ሂደትና በነፃነት መብት በማስጠበቅ ረገድ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

የምርጫ ስነ-ምግባር ደንቡ በጠቅላይ ሚኒስትሩና በሶስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪ ጥቅምት 20/2002 ዓ.ም መጀመሪያ የተፈረመ ሲሆን በኋላ ላይም በብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈርሟል፡፡ የልዑኩ የስነ-ምግባር ደንቡ የምርጫ ዘመቻ ለማካሄድ የጋራ ምክር ቤቶች ለማቋቋም ውይይትና ክርክር በፓርቲዎች መካከል ለማካሄድ እንዲሁም ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ሚና እንደሚኖረው ተገንዝቧል፡፡ ይሁን እንጂ የስነ-ምግባር ደንቡ እንደ ህግ መፅደቁ ደንቡን ባልፈረሙት ፓርቲዎች ጭምር ግድ ስለሚባል ትንሽ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

**የምርጫ አፈፃፀም**

በህገ-መንግስቱና በ2007 እ.አ.አ. በወጣው የምርጫ ህግ መሠረት የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ምርጫዎችን ለማካሄድ የህግ ማዕቀፎችን ለማውጣት የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ የምርጫ ቦርዱ በተወካዮች ምክር ቤት በተመረጡ ዘጠኝ አባላት ይመራል፡፡ ይህም የክልል፣ የዞንና የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት እንዲሁም 43,500 የሚጠጉትን የምርጫ ጣቢያዎችን ያካትታል፡፡

በአጠቃላይ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ የሆኑ ቴክኒካዊ ችግሮችን /ፈተናዎችን/ በማለፍ ምርጫውን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት አከናውኗል፡፡ የቦርዱ ምርጫ አስፈፃሚዎች የአሰራር ሂደቱን በሚገባ የሚያውቁና በአንፃራዊ በጥሩ ሁኔታ የደራጁ ነበር፡፡ ምንም እንኳ የሪሶርስ ችግር ቢስተዋልም የምርጫ ቦርድ ሰዎች ከሰራተኛውና ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ሲሆኑ በተቃዋሚዎች ዘንድ ስምምነት እምነት የማይጣልባቸው ነበሩ፡፡ ልዑኩ በምርጫ አስፈፃሚዎችና ክልል ባለስልጣናት እንዲሁም በገዢው ፓርቲ መካከል በተወሰነ ደረጃ አንዱ አንዱን ሆነው አግኝቷቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ ቦርድ አባል የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ሆኖ መገኘቱ በቅሬታ ጊዜ አድልዎ የሌለበት ውሳኔ ይሰጣል የሚል እምነትን እንደሚሸራርፍ ያሳያል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት /ጋዜጠኞች፣ ለህግ ባለሙያዎች፣ ለፖሊስ፣ ለሀገር ውስጥ ታዛቢዎች/ የተሰጠው ስልጠና ከምርጫ ቦርዱ በጐ ጐኖች አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለምርጫ አስፈፃሚዎች ከምርጫ ክልል  ባለፈ ምርጫ ጣቢያዎች አካባቢ  ላሉ ሰዎች የተሰጠው ስልጠና በልዑኩ እይታ በቂ አይደለም፡፡ ልዑኩ ከምርጫው ቀን በፊት የምርጫ ቁሳቁስ ጥበቃና እንክብካቤ ላይም ጥርጣሬ አለው፡፡

በአንድ የምርጫ ጣቢያ 1000 መርጮችን ለማስተናገድ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከ1997 የምርጫ ጣቢያዎች ቁጥር በ3% ወደ 43,500 ከፍ ብሏል፡፡ ይህም ጥሩ ዕድገት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በምርጫ ቦርድ የተሟላና ትክክለኛ የምርጫ ጣቢያ ዝርዝር አለመኖሩ የሂደቱን ግልፅነት አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡

እንደ ምርጫ ስነ-ምግባሩ አምስት የሕዝብ ታዛቢ በየምርጫው ጣቢያ መወከል አለባቸው፡፡ የእነዚህ ታዛቢዎች የስራ ሂደትም ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ግልፅ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን ይህ እንዳልተከናወነ በርካታ ሪፖርቶች ከተቃዋሚዎች መጥተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በታዛቢዎቹ ላይ ያለውን ጥርጣሬ አባብሶታል፡፡ ምንም እንኳ ታዛቢዎች ስልጠና የወሰዱ ቢሆንም ስልጠናቸው በቂ እንዳልነበረ በስራቸው ታይተዋል፡፡ በጠቃላይ የሕዝብ ታዛቢዎች መኖር ለምርጫው ግልፅነትና ተአማኒነት ያበረከተው ጉልህ ድርሻ የለም፡፡

ምርጫ ቦርድ ለልዑካኑ ያደረገው ድጋፍ በተለይ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጣም ጥሩ ነው፡፡

**የመራጮች ምዝገባ**

የመራጮች ምዝገባ ከጥር 5 እስከ የካተት 17/2010 እ.አ.አ. ተካሂዷል፡፡ ከአንድ ወር በኋላ ከተጀመረው ከሶማሌ ክልል በስተቀር መራጮች ከዚህ በፊት በተመዘገቡበት የምርጫ ጣቢያ ተመዝግበው ካርድ ወስደዋል፡፡

ከ37 ሚሊዮን ዕድሜው ለመራጭነት ከደረሰው ህዝብ 31,926,320 መራጮች እንደተመዘገቡ፤ በመጨረሻ ላይ የተያዘው የመራጭ ቁጥር ብዛት ያሳያል፡፡ ከ1997 ዓ.ም ሲነፃፀር የመራጩ ቁጥር በ5.5 ሚሊዮን ዕድገት አሳይቷል፡፡

ምንም እንኳ ሁሉን ያቀፈ የምዝገባ ሂደት ቢካሄድም ሂደቱ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት የጐደለው ነበር፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀ የመራጭ ዝርዝር የለም፡፡ አጠቃላይ ድምሩን ከማስቀመጥ ሌላ ተደራራቢ ምዝገባዎችንም ለማረጋገጥ ምንም አይነት ሁኔታ የለም፡፡ ካርዱ የጠፋበት መራጭ የምርጫ ጣቢያ አካባቢ ባሉ ሰዎች የሕዝብ ታዛቢዎች እንዲሁም የተከበሩ ሰዎች ማንነቱን ካረጋገጡ በኋላ የሚመርጥበት ሁኔታ ነበር፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች እንዲሁም የሰራዊቱ አባላት በተወለዱበት አካባቢ መርጠዋል፡፡ ነገር ግን በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡት መራጮች ቁጥር ብዛት 231,269 ነው፡፡ በሙቶ የሚቆጠሩ በነዚህ አካባቢዎች የምርጫ ኮሮጆዎችን ማቅረብና መሰብሰብ አዳጋች ከመሆኑም በላይ የአሰራሩን ግልፅነት የቀነሰ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ ቦርድ በነዚህ ልዩ አካባቢዎች ውስጥ ያሉትን የምርጫ ክልሎች ቁጥርና ዝርዝር ሁኔታ አላሳወቀም፡፡ ይህም ለታዛቢዎች የማይደረሱ ቦታዎች ምርጫ ተካሂዶ ይሆንን የሚል ጥያቄ አስነስቷል፡፡

**የእጩዎች ምዝገባ**

የእጩዎች ምዝገባ እ.አ.አ. በታህሳስ 25/2009 በምርጫ ክልሎች በሚገኙ ጽ/ቤቶች ተጀምሯል፡፡ ከዚያም ለብሔራዊ የጋራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ከፖለቲካ ፓርቲዎች በቀረበው ቅሬታ መሠረት ምርጫ ቦርድ የዕጩዎችን ምዝገባ ቀን ዕድሜ በ5 ቀን አራዝሞ እስከ የካቲት 22/2010 እ.አ.አ. አካሂዷል፡፡ በዚህ ረገድ በምርጫ ቦርድ የታየው ተግባር ከፍተኛ የሆነ የመድበለ ፓርቲ ስርአት እንደሰፈነ ያሳያል፡፡ እንደ ምርጫ ቦርድ መረጃ 2,174 ዕጩዎች ለተወካዮች ምክር ቤት 4,525 ዕጩዎች ደግሞ ለክልል ምክር ቤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ይህም ከ1997 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር የ15% እና የ19% ዕድገት አሳይቷል፡፡

ለዕጩዎች ምዝገባ የተቀመጠው መስፈርት አግባብ ያለውና ሁሉን ያሳተፈ ነበር፡፡ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረቡት 11 ቅሬታዎች በዕጩዎች ምዝገባ ላይ በተለይ ቋንቋን በተመለከተ በጥሩ ሁኔታ ታይቷል፡፡

በሶማሌ ክልል የመራጮችና የዕጩዎች ምዝገባ ለ21 ቀናት መጋቢት 19/2010 ጀምሮ ተካሂዷል፡፡ አንዳንድ በክልሉ የሚገኙ ፓርቲዎች እንደሌሎቹ ሁሉ በክልሉ የዕጩዎች ምዝገባ እንዲራዘም ጠይቀው ነበር፡፡ በክልሉ ለወካዮች ምክር ቤት የሚካሄደው ምርጫ እንደሌሎቹ ግንቦት 15 የተፈፀመ ሲሆን ለክልሉ ምክር ቤት የሚካሄደው ምርጫ ደግሞ ግንቦት 22 እንዲካሄድ ተወስኗል፡፡

በሶማሌ ክልል ዘግይቶ የተጀመረው የዕጩዎች ምዝገባ በክልሉ የተካሄደውን የምረጡኝ ዘመቻ ዕድሜ በጣም ወስኖታል፡፡ ምንም እንኳ ምርጫው በሰላማዊ መንገድ የተካሄደ ቢሆንም የእኩልነት መርህ በዕጩዎች ምዝገባና የምረጡኝ ዘመቻ ረገድ በትክክል አልተተገበረም፡፡

እንደ ምርጫ ቦርድ መረጃ 72 ዕጩዎች በዛቻና ማስፈራሪያ እንዲሁም በገንዘብና በሌላ የግል ችግር ምክንያት እራሳቸውን በምርጫ ዘመቻው ወቅት አግልለዋል፡፡ ይህም የመራጮች የፈለጉትን የመምረጥ ዕድልና የተወካዮች አማራጭ መኖርን በአንዳንድ የምርጫ ክልሎች ቀንሶታል፡፡

## የምረጡኝ ዘመቻ

በየካቲት 9/2010 የጀመረው የምረጡኝ ዘመቻ በጠቃላይ ሰላማዊ ነበር፡፡ ቀዝቀዝ ብሎ ሲካሄድ የነበረው ዘመቻ በማብቂያው አካባቢ ሞቅ ደመቅ ብሏል፡፡ የቤት ለቤት ቅስቀሳው በሁሉም ፓርቲዎች በብዛት የሚታይ ነበር፡፡

ይሁንና በርካታ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ከገዢውም ከተቃዋሚ ፓርቲዎችም በዘመቻው ወቅት ተሰምቷል፡፡ በተለይ በተከለከሉ ቦታዎች ዘመቻውን ለማካሄድ በሚሞከርበት ጊዜ በርካታ ክሶች የሚመጡት ከተቃዋሚዎች ነበሩ፡፡ ከክልል ባለስልጣናት ከገዢው ፓርቲና ከፖሊስ ከፍተኛ ፈተና እንደገጠማቸው በተለይ የምርጫው ቀን እየቀረበ ሲመጣ እንደባሰ ገልፀዋል፡፡ በአፋር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልል በሚገኙ የምርጫ ክልሎች ተቃዋሚዎች የምርጫ ዘመቻ ለማካሄድ ከቀበሌ መስተዳድሮች ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸው ከዚህ ጋር በተያያዘ 27 ሰዎች እንደታሰሩ ተገልጿል፡፡ ተቃዋሚዎች ያካሄዳቸው ሰልፎች የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት በቀረፀው ፊልም መሠረት ልዑካኑ ፊልሙን ተመልክቶ የማስፈራሪያ ምልክት እንደሆነ ተገንዝቧል፡፡

ከተቃዋሚዎችም ዘገገር ፓርቲም የሚመጡ የማስፈራሪያና የዛቻ ክሶች ወደ መጨረሻ ሳምንቶች አካባቢ እየጨመሩ መጥተው ነበር፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ሲከስ ተቃዋሚዎች ግን ገዢውን ፓርቲን፣ የክልል ባለስልጣናትንና የፖሊስንም ጭምር ከሰዋል፡፡ ይህም ለጠቅላላው የምርጫ ሂደት ግምገማ ግብአት ይውላል፡፡ ይህ ሲባል ድርጊቶቹ ከግለሰቦች የመነጩ አለመሆናቸው ምንም አይነት ማስረጃ የለም፡፡ ልዑካኑ የምርጫው ዘመቻ በዛቻና ከማስፈራሪያ ነፃ ሆኖ እንዲከናወን የተወሰደው እርምጃ አናሳ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በተቃዋሚዎች ዘንድ የገንዘብ ማነስ አነስተኛ ዘመቻ እንዲያካሂዱ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ ምንም እንኳ መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረበው የገንዘብ ድጋፍ ጥሩ ቢሆንም ገንዘቡ ውጤታማ ዘመቻ ለማካሄድ በቂ አልነበረም፡፡ ዘግይቶ ክፍፍል መደረጉም ሌላው የሚተች ጎኑ ነው፡፡ ከሌሎቹ ሲነፃፀር ኢህአዴግ ከመንግስት ከሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ ጥገኝነቱ አነስተኛ ነበር፡፡ ፓርቲው ከአባላቱና ከግለሰቦች ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እርዳታ አግኝቷል፡፡

ልዑካኑ ገዢው ፓርቲ የሕዝብ ሀብትን ለፓርቲ ዘመቻ እንዳዋለው ተመልክቷል /በተለይ በአማራ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊያ ክልል እና ተግራይ/ እንዲሁም በመንግስትና በገዢው ፓርቲ መካከል ልዩነት አይታይም ነበር፡፡ ይህም አግባብ ያልሆነ የመንግስትን ሀብት መጠቀም ገዢው ፓርቲ የማይገባውን ጥቅም እንደወሰደና ያልተስተካከለ የመጫዋቻ ሜዳ ለሁሉም ፓርቲዎች መኖሩን ያሳያል፡፡

**የመገናኛ ብዙሃን ሁኔታ**

---

መገናኛ ብዙሃኖች የዋና ዋና ፖለቲካ ፓርቲዎች ቅስቀሳ በሚገባ ዘግበዋል፡፡ የመንግስትም ሆኑ የግል ሚዲያዎች የመራጩን ግንዛቤ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ በጋዜጣና ኤሌክትሮኒክስ ሚደያዎች የሚተላለፉ መረጃዎች በመላ ሀገሪቷ አለመዳረስ ህብረተሰቡ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ምርጫ እንዳያደርግ አስችሎታል፡፡ የVOA አማርኛው ሰርጭት በሀገሪቷ መታፈኑ መራጮች ከተለያዩ ምንጮች መረጃ እንዳያገኙ ከልክሎአቸዋል፡፡

ምርጫ ቦርድና የመንግስት ተቋማት ነፃ የአየር ሰአት ለ63ቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች በተወካዮች ምክር ቤት እንዳላቸው ውክልና እና እንደ ዕጩዎቻቸው ብዛት ሰጥተዋል፡፡ ምንም እንኳ ብዙዎች በዚህ ቢስማሙም ጥቂቶች ብቻ ዕድሉን ተጠቅመዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዋና ዋና የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል በሀገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በብሔራዊ ሚዲያዎች ዘጠኝ ዙር ክርክሮች ተላልፈዋል፡፡ ምንም እንኳ ያልሆኑ መልእክቶች በቀጥታ እንዳይተላለፉ የቀጥታ ስርጭት ባይሆንም ውይይቱና ክርክሩ የሚመሰገን ድርጊት ነው፡፡

ምንም እንኳ በገለልተኝነት ቢቀርብም የመንግስት ሚዲያዎች ሚዛናዊ የሆነ መረጃን ለማቅረብ ተስኗቸዋል፡፡ በአብዛኛው ሪፖርታቸው የገዢውን ፓርቲ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በተለይ ወደመጨረሻዎቹ የዘመቻ ቀናት ኢህአዴግ ከ50% በላይ በዜና ሽፋን አግኝቷል፡፡

የግሉ ኘሬስ ሰፊ ባሉ የፖለቲካ አይታ ውስጥ ተንቀሳቅሷል፡፡ ባጠቃላይ ልዑካኑ  የኢትዮጵያ ሚዲያዎች በምረጡኝ ዘመቻ ወቅት የተካሄደውን እንቅስቃሴ በጥሩ ሁኔታ የዘገቡ ሲሆን የመንግስት ጋዜጠኞች በጥንቃቄ ከመንግስት ስራቸው ጋር በማያጋጫቸው መልኩ ሲዘግቡ ነበር፡፡

ምንም እንኳ የምርጫ ዘመቻው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚዲያዎች ሚና ምን እንደሚመስል በግልፅ የሚያስቀምጥ ህግ ባይኖርም ምርጫው ከመድረሱ በፊት በነበረው በ48 ሰአት ውስጥ የመንግስትም ሆነ የግል ሚዲያዎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን መልእክት ሲያስተላልፉ ሽፋን ሲሰጡ ነበር፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ የሚዲያ  ሕግ ጋር የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከምርጫ ቀን በፊት የነበረው የዕረፍት ቀን ለመራጩ ሕዝብ የአማራጭ ጊዜ ነበር፡፡

**ሰብአዊ መብትና ሲቪል ማህበራት**

የፖለቲካ መብትና መሠረታዊ ነፃነትን ማክበር ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት አለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶችንና የሰብአዊ መብት አያያዝን ያካተተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በቅርብ ጊዜ የወጡት በርካታ ህጐች ለምሳሌ ፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ፣ የመገናኛ ብዙሃንና መረጃ የማግኘት ህግ፣ እንዲሁም የበጐ አድራጊዎችና የሲቪል ማህበራት ህግ በህገ መንግስቱ ውስጥ የተካተቱትን መብት ለማግኘት የሚያስችሉ አይመስሉም፡፡

ልዑካኑ በተለይ በአንዳንድ ገጠራማ አካባቢዎች እንዳስተዋለው የመንግስት ባስልጣናት በአስተዳደራቸው ለግለሰብና ለፖለቲካዊ መብቶች ምቹ አይደሉም፡፡ በነፃነት የምርጫ ዘመቻ ማካሄድና ሌሎች መሠረታዊ ነፃነቶች የመሰብሰብ ነፃነት የመናገርና የመንቀሳቀስ ነፃነቶች በወጥነት አይበቁም፡፡ በተለይ ምርጫው እየቀረበ ሲመጣ ይህም የፖለቲካ ፓርቲዎችና እጩዎች ለዘመቻ ያላቸውን እኩል ሁኔታ የሚያንገጫግጭ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳ ጠቅላላ የምርጫው ውጤት ይፋ እስከሚሆን ዕጩዎች እንደማይታሰሩ ህግ ቢኖርም ልዑካኑ ስድስት የተቃዋሚ ዕጩዎች መታሰራቸውን ደርሶበታል፡፡ በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎች ያለምንም ክስ መታሰራቸውን ለልዑኩ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ የቅንጅት መሪ የሆኑት ወ/ት ብርቱካን የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸዋል፡፡ ፓርቲያቸው ፎቶአቸውን በመያዝ በምርጫው ዘመቻ ወቅት እንዲፈቱ ጠይቋል፡፡ ብርቱካን በ1997 በሌሎች ተቃዋሚ መሪዎች ጋር የታሰሩ ሲሆን ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለማፍረስ በመሞከር የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበቸዋል፡፡ በ1999 ምህረት ቢደረግላቸውም ተመልሰው ታስረዋል፡፡ ምክንያቱም ምህረቱን በመካዳቸው ነው፡፡ ይህም አወዛጋቢ ጉዳይ ነው፡፡

አዲሱ የኢትዮጵያ የበጐ አድራጊዎችና የሲቪል ማህበራት ህግ የሲቪል ማህበራት ሚናን በምርጫ ሂደት ውስጥ አድርጐታል፡፡ የውጪ ገንዘብ ዕርዳታንም ከማህበራቱ ጠቅላላ ገቢ 10% ብቻ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ከ10% በላይ የውጪ እርዳታ የሚያገኙ ከሆኑ ማህበራቱ ኢትዮጵያዊ ማህበራት አይደሉም፡፡ ይህም በሰብአዊ መብቶችና ዴሞክራሲያዊ ጉዳዮች ላይ እንዳይሰሩ ይከለክላቸዋል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት የመራጮች ትምህርትና የሀገር ውስጥ የታዛቢነት ስራ እንዳይሰሩ ገድቧቸዋል፡፡

**የሴቶች ተሳትፎ**

እንደ ምርጫ ቦርድ ጠቅላላ ከተመዘገበው ሕዝብ 48.22 ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም ከጠቅላላው ሕዝብ ብዛት ሲታይ ትንሽ አለመመጣጠን ያሳያል፡፡ ምንም እንኳ በምርጫ ጣቢያዎች በርካታ ሴቶች ቢታዩም በምርጫ አስተዳደር ላይ አነስተኛ ቁጥር ነው የላቸው፡፡ በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥም ቁጥራቸው አነስተኛ ነው፡፡ በ30% ኮታው መሠረት ኢህአዴግ የሴቶችን ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ላይ ነው፡፡

ምንም እንኳ ብዙ ሴቶች በፖለቲካ ፓርቲዎች ባይኖሩም ለሴት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊሰጥ የተወሰነው ከፍ ያለ የገንዘብ እርዳታ በጣም ጥሩ ተግባር ነው፡፡ እንደምርጫ ቦርድ ከሆነ ከ2,174 የተወካዮች ምክር ቤት ዕጩዎች 11%ቱ ከ4,525 የክልል ምክር ቤቶች ዕጩዎች 15%ቱ የሴቶች ናቸው፡፡ ይህም ከ1997ቱ ጋር ሲነፃፀር የሴቶች ተሳትፎ ቀንሶ ይገኛል፡፡ በፊት በተወካዮች ምክር ቤት 15% ሲሆን በክልል ምክር ቤቶች ደግሞ ተሳትፎአቸው 23% ነበር፡፡ እንደ ምርጫ ቦርድ ይፋ መረጃ የሴቶች ዕጩዎች ተሳትፎ ከክልል ወደ ክልል ይለያያል፡፡ ለምሳሌ በቤንሻንጉል ጉሙዝ 8% የሚሆኑት ዕጩዎች ሴቶች ሲሆኑ በአዲስ አበባ 20% የሚሆኑት የተወካዮች ምክር ቤት ዕጩዎች ሴቶች ናቸው፡፡

**የመራጮች ትምህርት**

---

የምርጫ ቦርድ ቁሳቁሶችን አዘጋጅቶ በክልልና በዞን ጽ/ቤቶች እንዲሁም በመገናኛ ብዙሃን፣ በድራማና በፖስተሮች አሰራጭቷል፡፡ በተግባር የክልል አስተዳዳሪዎች የማህበረሰብ መሪዎች በተወሰነ ደረጃ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ የመረጃ ምንጭ ሆነው አገልግለዋል፡፡

**የሀገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች**

---

ምርጫ 2002 ለመታዘብ ከተሰማሩት ውስጥ ዋነኛው 11 ማህበራትን ያቀፈው የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ጥምረት ምርጫ ታዛቢ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ዋነኛው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ነው፡፡ ጥምረቱ 40,000 ታዛቢዎችን ያቀፈና በመላ ሀገሪቷ ያሰማራው ነበር፡፡ ግንቦት 16 ምርጫው በሰላማዊ መንገድ መካሄዱን በመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርቱ ገልጿል፡፡ ሌሎችንም የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ፈቃድ አግኝተው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንም/ኢሰመኮ/ ምርጫውን ታዝቧል፡፡ ሁሉም የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ድምዳሜያቸውን በአንድ ወር ውስጥ ይፋ እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡ ይህም የምርጫ ታዛቢነት ስራው ነፃነትና ገለልተኝነት ላይ ጫና ያሳድራል፡፡ ተአማኒነት ያለበትና ውጤታማ የሆነ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት ስራ ግልፅነት የሰፈነበት የምርጫ ሂደት ለማካሄድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በኢትዮጵያ ከምርጫ ጋር በተያያዙ የሚመጡ ቅሬታዎችን ለማየትና ለመፍታት ሶስት መዋቅሮች ተዘጋጅተዋል፡፡

1. ፍርድ ቤት /በመጀመሪያ ደረጃ ችሎት ወይም በይግባኝ/
2. ሰምርጫ አስተዳደር /በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በኩል/
3. የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት /ጉዳዩን የሚያይ ግን ለፍርድ ቤት የሚያቀርብ/

የድምፅ አሰጣጥን የተመለከቱ ቅሬታዎች ምርጫ ጣቢያ በሚገኙ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች መቅረብ አለበት፡፡ ቆጠራና ውጤትን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ48 ሰአት ውስጥ በምርጫ ክልል ለሚገኝ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መቅረብ ይችላል፡፡ የሁሉም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ውሳኔዎች ለአዲስ አበባ ምርጫ ቦርድ ሊቀርቡ ወይም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ባልተመሰረተባቸው አካባቢዎች ጉዳዮን በክልሉ የምርጫ ጽ/ቤት ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እስከ አሁን ልዑካኑ 204 የሚሆኑ ጉዳዮችን ለምርጫ ቦርድ አቅርቧል፡፡ 113ቱ ከምርጫ ዘመቻ ጋር የተገኙ ናቸው 45ቱ ደግሞ ዕጩዎችንና ደጋፊዎችን በመደብደብና በማስፈራራት የቀረቡ ናቸው፡፡ እስካሁን 90 የሚሆኑ ጉዳዮች እልባት አግኝተዋል፡፡ ለግልግል ወይም ጉዳዩን ወደ ፖሊስና የጋራ ምክር ቤቶች በመምራት ጉዳያቸው ታይተዋል፡፡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት የዕውቀት ደረጃ ግን ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ተአማኒ የሆነ የቅሬታ እልባት ሰጪ ስርአት ለማስፈን ይህ ችግር መታየት አለበት፡፡

የተቃዋሚዎች በፍርድ ቤቶችና በፖሊስ ገለልተኛ አለመሆን ላይ ያላቸው ጥርጣሬ ከምርጫ ጋር በተያያዙ ለሚከሰቱ ቅሬታዎች መፍትሔ እንደማይኖራቸው ነው የሚያመለከተው፡፡ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ ጉዳዮችም እንደማይኖራቸው ነው የሚያመላከተው፡፡ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ ጉዳዮችም አነስተኛ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ በጋራ ምክር ቤቶችና በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች እየታዩ ናቸው፡፡ አንዳንድ የጋራ ምክር ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ችሎት እንደመሆናቸው /በጊዜያዊነት/ ወንጀል ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ተቀብለው ወስነውባቸዋል፡፡

በተለያዩ ቦታዎች የምርጫ ፖስተሮችና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጠፉ ሰዎች እስከ 10 ወር የሚደርስ የቅጣት ብይን የተሰጠበት ሁኔታ አለ፡፡ ያለምንም በቂ ጊዜና ለመከላከል ዕድሉ በሌላቸው ሁኔታ ልዑኩ ይህንን ተገቢ እንዳልሆነ ተገንዝቧል፡፡ በዚህ ዙሪያ እስካሁን 76 የሚደርሱ በገዢው ፓርቲ የቀረቡ ክሶች ለፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 61 የሚሆኑ በሁለት ቀናት ውስጥ መፍትሔ አግኝተዋል፡፡

ብዙዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅሬታዎችን ለማሰማት ሲሉ በጋራ ምክር ቤቱ ተሳትፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ ምክር ቤቶች በመላ ሀገሪቱ በወጥነት አልተመሰረቱም፡፡ በአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የተሳትፎ ሁኔታ የቀነሰ ነበር፡፡

**የድምጽ አሰጣጥ ቆጠራና ድምር**

የምርጫው ዕለት ሰላማዊና ሕዝቡ በነቂስ የተሳተፈበት ነበር፡፡ የምርጫው ሚስጢራዊነትም የጠበቀ ነበር፡፡ ልዑካኑ አንዳንድ ችግሮችና በአሰራር ሂደት ወጥነት ዙሪያ እንከኖች እንደነበሩ ታዝቧል፡፡

ቡድኑ የመከፈቻውን ሂደት 83% በሆነው በታዘበበት የምርጫ ጣቢያዎች በታዘበው መሠረት ጥሩ ወይም አጥጋቢ በማለት መድቦታል፡፡ 23%በሚሆኑ ልዑኩ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የመጡት የኮሮጆዎች ብዛት ግን የምርጫ ቦርድ በላከው ሰነድ

መሠረት የተረጋገጡ አይደሉም፡፡ 34% በሚሆኑ ልዑኩ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገበው መራጭ ለፓርቲ ተወካዮች አልተገለጠም፡፡ የምርጫ ጣቢያ ኮሚቴዎች በደንብ የተደራጁና በአሰራር ሂደታቸው ጥሩ እውቀት ነበራቸው፡፡

በአጠቃላይ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት የታዛቢው ቡድን የደረሰባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉ ጥሩ ነበር፡፡ በ87%ቱ ሂደቱ ጥሩ 13% አጥጋቢ ነበር፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች ነበሩ፡፡ የኢህአዴግ ተወካዮች በአብላጫ ነበሩ፡፡ የመድረክ በግማሽ ገደማ የመኢአድ ደግሞ 21% ገደማ ነበሩ፡፡ በ76% የምርጫ ጣቢያዎች የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ተገኝተዋል፡፡ አብዛኞቹ ከጥምረት የመጡ ነበር፡፡ ሴቶች ከድምፅ መስጫ ጣቢያ ኮሚቴ አባላት 28%ቱን ይይዛሉ፡፡ ከከሚቴዎቹ 11%ቱ ብቻ በሴቶች የሚመሩ ነበሩ፡፡

ልዑካኑ በደረሰባቸው 21% በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ሰዎች ያለምርጫ ካርድ እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ 15% በሚሆኑ ጣቢያዎች የምርጫ ካርድ ማስወገድ ስራ ጥሩ አልነበረም፡፡ ይህንን በተመለከተ የምርጫ ቀለም ምልክት ሁለትና ከዚያ በላይ ጊዜ የመምረጥ ዕድልን ለማስቀረት በትክክል መደረግ ነበረበት፡፡ ቡድኑ በመራጭ ስም አመዘጋገብና በፊርማ አለመመሳሰል ዙሪያ ችግሮችን ተመልክቷል፡፡ 13%በሚሆኑ የቡድኑ የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮችን ውሳኔ ለማስቀየር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በአካባቢው ታይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከጥቂት ቅሬታዎች በስተቀር የምርጫ ፍፃሜና ቆጠራ በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡ በ64% በሚሆኑ ጣቢያዎች ጥሩ ወይም አጥጋቢ የሚያስብል ውጤት ሲገኝ በ34%, በሚሆኑ ጣቢያዎች ውጤቱ ሂደቱ ዝቅተኛ ነበር፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ ተዛቢዎችና የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች በቆጠራው ጊዜ ነበሩ፡፡ ይህም 75% ሰሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ተስተውሏል፡፡

የምርጫ ህግ እንደሚለው ድምፅ እንዲቆጠር የ X ምልክት ወይም የአውራ ጣት አሻራ መጠቀም ነው፡፡ ልዑካኑ ለመራጩ ጥርት ያለ ሃሳብ ትምህርት መሰጠት እንዳለበት ያምናል፡፡ ተቀባይነት ያለውን ድምፅ አሰጣጥ መለየት ችግር የለውም በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ያሉት በትክክል የመራጩን ሐሳብ ከተረዱትና በትርጓሜው ከተስማሙ፡፡

በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራው ሂደት ችግር ነበረበት፡፡ በስርጭት ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆኑትን ድምፆች የመለየት ችግር ነበር በ25% በሚሆኑ ጣቢያዎች የውጤት መግለጫ ወረቀቱ ለፓርቲ ተወካዮች አልተሰጠም፡፡ በግማሽ በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት በይፋ አልተለጠፈም፡፡

እንደ ምርጫ ቦርድ የመጨረሻው ውጤት ሰኔ 14/2002 ዓ.ም ይፋ ይሆናል፡፡ ቡድኑ የቆጠራውንና ቀጣይ ሂደቶችን ይከታተላል፡፡